# በየመን ያለን ኢትዮጵያዊያን ስጋት አርግዘን ስጋት ለብሰናል

በግሩም ተ/ሀይማኖት

በየመን ያለ ሀበሻ ቁጥሩ ሲጠራ የሚያምን የለም:: ትክክል የማይመስል ነገር ነው:: በህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ ሁኔታ የመን ውስጥ ያለ ኢትዮጵያዊ ከ80,000 በላይ ነው:: 5000 የምንጠጋው በUNHCR ስር ያለን ስንሆን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለማቋረጥ እና የመን ለመኖር ከጅቡቲ ... ከሱማሊያ ... ተነስተው በባህር በየእለቱ የሚገቡትን መገመት ይከብዳል:: ከ4,000,000 በላይ ትውልደ ሀበሻ አለ:: ከአረብኛው ቀጥሎ ህዝቡ በሰፊው የሚናገረው አማርኛ ቋንቋ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ የሚያሳየው የመናዊያን እና ኢትዮጵያዊያን አብረው የኖሩ ህዝቦች መሆናቸውን ነው:: ነገር ተገልብጦ ሆኗል:: ትላንት ችግራቸውን ለመቅረፍ ወደ ሀገራችን እንዳልተሰደዱ፣ ለሀበሻ ያላቸው ጥላቻ ኢትዮጵያን እጇ ሰባራ ያሰኛታል:: ለነገሩ እንኳን የተጠለለባት ከአብራኳ የወጣውስ ነካሽ እንጂ አይዞሽ ባይ መች ሆናት? ... ቢሆን ኖሮ ከነቀዞች ማላቀቂያው ሰዓት አሁን ነበር::

የመን ስላለ ሀበሻ ይህን ያህል ካልኩ ወደ ተነሳሁበት የስጋት መስመር ላቆልቁል:: በአረቡ አለም እየተቀጣጠለ ያለው የለውጥ ማዕበል ማነው ባለተራ እያለ የሚያዳርስ ይመስላል:: ወጉ አይቅርብኝ ብለው ነካ ... ነካ ... የሚያደርጉ ሀገራትም አልጠፉም:: እኛ በስደት ከእጅ አይሻል ዶማ ኑሮ የምንኖርባት የመን አንዷ የእንቅስቃሴው ማዕበል የሚያናውጣት ነች:: የመፋጠጡን ነገር ተውኝ:: ተፋጠዋል ... እኛም ሊመጣ የሚችለውን ችግር አስበን ስጋት አርግዘን ... ስጋት ለብሰን ... በስጋት አንሾካሾክን ነው ያለነው:: ለ32 አመታት ሀገሪቷን ሲመሩ የነበሩት አሊ አብደላ ሳላህን ከስልጣን እንዲለቁ የሚጠይቁ ወገኖች ብቅ ካሉ ሳምንታትን እያስቆጠሩ ነው:: በዛው መጠን ደጋፊዎቻቸውም "ማፊሽ አህሰን አሊ አብደላ ሳላህ!!" የሚል የዘውትር መፈክራቸውን እያሰሙ ፎቶ ይዘው አደባባይ ይውላሉ::" ... "እንደ አሊ አብደላ ሳላህ ጥሩ የለም" ማለት ነው:: ይህ በሰነዓ ነው:: በትእዝና በአደን ደግሞ ከዚህ የተለየ አመጹ የከፋና ሰልፍ የሚወጡትም ቁጥር የበዛ ነው:: በተለያየ ቦታ ውጥረት ውስጥ ያለችው የመን የእርስ በእርስ ጦርነቱ ረገብ በማለቱ ህዝቡ ተደስቶ ነበር:: አሁን ከቱኒዝ የተነሳው የአመጽ ማዕበል ግብጽን ... የመንን፣ ጆርዳንን ... ሊቢያንን፣ ባህሬንን ... ሳዑዲን ... አማንን ... መነካካቱ የሚታወቅ ነው:: የመን በዩንቨርስቲ ተማሪዎች የተጀመረው ሰላማዊ ሰልፍ በቶሎ እንዲበርድ ፕ/ት አሊ አብደላ ሳላህ አስበው በዩንቨርስቲ ውስጥ የሚከፈለውን ክፍያ ከመቀነስ ጀምሮ በነጻ እስከማድረግ ያለ እርምጃ ወስደዋል::

የሀገሪቷ ፕሬዚዳንት የስልጣን ዘመን ማብቂያ 2013 ነው:: ፕሬዚዳንት አሊ አብደላህ ሳላህ ከ30 አመት በላይ አስተዳድረዋል:: ሀገሪቷን አሳድገዋታል የሚሉ ሞልተዋል:: ምን ያሳድጋታል ኑሮው ከፋ የሚሉት ሕዝቡ ሁኔታው እና ያለው ችግር ፈንቅሎት ነው ተቃውሞ የወጣው የሚሉ ናቸው:: መንግስት ሰሞኑን በተቃዋሚዎቸ የተደረገውን የሰላማዊ ሰልፍ ሙከራ በማየት 10% የደሞዝ ጭማሪ ለወታደሩ ክፍል፣ 4% ደግሞ ለመንግስት ሰራተኞች ጭማሪ ቢያደርግም ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር ተነጻጻሪ አይደለም የሚሉ ወገኖች አሉ:: ሁኔታው ለፕሬዚዳንት አሊ አብደላ ሳላህ አሳሳቢ ስለሆነ እንደሆነ የደሞዝ ማሻሻያ ያደረጉት ተቃዋሚዎችም ሆነ የመገናኛ ብዙሀን ይጠቅሳሉ:: ፕሬዚዳንቱን ለ2011 ማብቂያ ስልጣናቸውን እንዲለቁ የጠየቁት ተቃዋሚዎች ሰነዓ ውስጥ ዳይሪ የሚባል ዩንቨርስቲው ያለበት አካባቢ ድንኳን ጥለው ሲቀመጡ የፕሬዚዳንቱ

ደጋፊዎችም ያንኑ አድርገው ፊት ለፊት ተፋጠዋል:: አሁን አሁን የድንኳኑም መጠን እየጨመረ ነው:: ታህሪር የሚባለው ቦታም እንዲሁ የፕሬዚዳንቱ ደጋፊዎች ድንኳን ጥለው ተቀምጠዋል:: ትላንት እ. ኤ. አ. በ08/03/2011 ማታ ላይ ስለሁኔታው ለማወቅ ሄጄ ሳለ ድንኳን የጣሉበት ቦታ መጠን ጨምሮ አካባቢው በሰው ተጨናንቆ መንገድ ተዘግቶ አየሁ::የሚገርመው ደግሞ ዝግጅታቸው ተጠናክሮ ድንኳኖቹ ውስጥ ለምሽግ ይሁን ብርድ ለመከላከል ባላወኩት ሁኔታ በብሎኬት ግንብ ይገነባል:: ያለው የጥበቃ ሁኔታም እየተጠናከረ ፍተሻው እየከበደ ነው:: ያሳስባል፣ አስጊ ነገር አርግዟል:: ደጋፊዎቹ ምግብም ሆነ የቀን ወጭ ተችለው እንደሆነ የተቀመጡት ተቃዋሚዎች ይናገራሉ:: ይህ ህዝቡ ሁሉ የሚያውቀው ነገር ነው::

በየመን ካለው የውጭ ዜጋ ከብዛት አንጻር ተጎጂ የሚሆነው ሀበሻ እንደሆነ ይታወቃል:: ኤምባሲውም ባለፈው አርብ ህዝቡን ሰብስቦ "..በጊዜ ወደቤት ግቡ...." ብሏል::

"ሰውየው ንግግር አደርጉ ..." ያሉት ትናንሽ ጥቅማ ጥቅም ናፋቂዎች ወደ ኤምባሲ እየቃረሙ የሚወስዱትን ወሬ ጥለው የኤምባሲውን ለእኛ ሲያቀብሉ "... በጊዜ ወደቤት ግቡ ሞባይላችሁን ካርድ ሞልታችሁ አስቀምጡ አደጋ ወይም ችግር ሲገጥማችሁ ወዲያው ደውሉ ... ኮሚኒቲ ተመዝገቡ ... ችግር ቢነሳ እንኳን ኢትዮጵያዊነታችሁ ታውቆ ወደ ሀገር እንድትገቡ ..." አሉ አዲሱ ቆንስላ ሲሉ አበሰሩን። ጽድቁ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ ይላሉ አባቶች:: በሞባይል ተጠርተው ሊደርሱ አይደለም፣ ግፍ የሚፈጸምባቸው ዜጎቸ ኤምባሲ ሄደው አቤት!!! ... ሲሉ እኛ ለገረድ አልመጣንም ማለታቸው ያቆሰለው ሁሉ አረ!! ... ዛሬ ምን ታያቸው? ገንዘብ ፈልገው ይሆን? ሲል ተደምጧል:: ኮሚኒቲ ለመመዝገብ ፓስፖርት ወይም መታወቂያ የሚያስፈልግ ሲሆን ያ-ካለ ኮሚኒቲ መመዝገቡ ለምን አስፈለገ? ኢትዮጵያዊነትን አይገልጽም?

አንደኛ አልቀርብ ያለውን ህዝብ ወደ ኤምባሲውና ኮሚኒቲው ማቅርቢያ መንገድ ነው ፍላጎታቸው:: ምንም እንደማይጠቅማቸው ያወቁትን ኤምባሲ ቅንጣት እምነት አይጥሉበትም:፣ የተበደሉ ወገኖች እንኳን ሲግጥም ... ኩሩቤል ጋር ሂዱ ነው የሚባለው:: ማንም ኤምባሲ ሂድ አይልም:: ኩሩቤል ማነው? ትሉ ይሆናል፣ ዛሬ ርዕሴ ስላልሆነ በቀጣይ ከunhcr ጋር በተያያዘ እመለስበታለሁ::

ሁለተኛ፣ 3000 ሺ.ህ የነበረውን ቀንሰን በ2000 የየመን ሪያል እያሉ እያስከፈሉ ስለሆነ የሚመዘግቡት ለጥቅም ሲሉ ነው እያለ ስደተኛው ሲያማርር ተሰምቷል:: መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል ነው:: ሁሉን መሸጥ የለመደ መንግስት ጭፍራ ሆነው ሌላ ምን ያርጉ? እዚህ ያሉ እህቶች ያሳዝኑኛል:: በጉለበታቸው ፋገው ያመጡትን ዝቅተኛ ክፍያ ሊበላቸው ያሰፈሰፈው ብዛቱ ... ዳላላው፣ መኖሪያ ፍቃድ አስሪው ... የትዳር ጭንብል ያጠለቀው ወንድ ... ኤምባሲው ... ብቻ ሁሉ የያዘትን ሊያራግፋቸው ነው የሚጥረው:: በእርግጥም አራግፈው መታከሚያ ... ሀገር መግቢያ የሚያጡ ሞልተዋል::

ማንም በኤምባሲው እምነት አላሳደረም:: ምክንያቱም ከዚህ በፊት ኤምባሲው ለዜጋው ምንም ሲያደርግ አይታወቅም:: ከ80 ሺ.ህ በላይ ዜጎች ያሉት ኤምባሲ የቀብር ቦታ ጥይቆ ያላዘጋጀ ዜጋው ሲሞት ለመቅበር ቦታ ጥፍቶ በየፍሪጅ ውስጥ ሬሳ ሲበሰብስ ዝም የሚል ኤምባሲ ... ተበደልን ሲባል የራሳችሁ ጉዳይ የሚል ኤምባሲ ... ዜጎቹ የመኖሪያ ፍቃድ ማሰሪያ ቦታ አጥተው ጀበሀ የሚባል የኤርትራ

ተቃዋሚ ቡደን የየመንን መንግስት አስፈቅዶ ማሰራት ሲጀምር ... ብሎም ከ5000 በላይ ኢትዮጵያዊያን ከ100-300 ዶላር ተበልተው ሲቀሩ ምን አገባን ያለ ኤምባሲ ሞባይላችሁን ካርድ ሙሉ የሚሉት ቢጠሩ ሊመጡ ነው? ሁሉን ያነጋገረ ጉዳይ ነበር:: የቀብር ቦታ እንኳን ከቻይኖች ጋር ጥገኛ ሆነን ነበር:: እነሱም ከልክለው የተቀበረውንም የሀበሻ ሬሳ አውጥተው ሲጥሉ ዝም ያለ ኤምባሲ ቢደወልለት ይደርሳል? እዚህ ያለ ሀበሻ በሙሉ የሚያውቀው ነገር አለ። ሲሞት የመስሊም ስም እየተቀየረለት ነው የሚቀበረው:: ይህን ኤምባሲውም ያውቃል::

ውጥረቱ ያየለበት ምስኪን ስደተኛ ወደ UNHCR ቢሮ ብቅ ቢልም ተስፋ አስቆራጭ ምላሽ አግኝቶ ተስፋው ጭልሞበት ስጋት ባቻ ሳይሆን ፍርሀቱም አይሎበት እንዳለ .... አለ:: "... ምንም ልናረግላችሁ አንችልም:: ባለው ሁኔታ ሁለት ቦታ ቢሯችንን ዘግተናል:: የከፋ ነገር ቢምጣ እዚህ ያለውን ቢሮም ዘግተን እንሄዳለን:: ባጀት ስለሌለን ዘግተን ከመሄድ ውጭ ምንም ልናረግላችሁ አንችልም:: ..." ለሚመለከተው ሁሉ አቤት ቢባል ምላሽ የለም::

እዚህ ያለ ሀበሻ የየመን ፖለቲካ አይደለም ችግሩ:: ሀገርስ ቢገባ የሚጠብቀው ምንድን ነው? ብዙውም አሁን ያሉት ፕሬዚዳንት አሊ አብደላ ሳላህ እንዲቀጥሉ ነው ፈጣሪውን የሚለምነው:: ምክንያቱም ህዝቡ ለሀበሻ ያለው አመለካከት ጥሩ ስላልሆነ ችግር ቢነሳ ይጨርሱናል የሚል ፍርሀት አለው:: በእርግጥም ሀቅ ነው:: ሼህ የሚባሉ የጎሳ መሪዎች አሉ። እያንዳንዳቸው የታጠቀ ሰራዊት አላቸው:: ለሀበሻ ፍርሀቱ ብዙ ነው:: የምናሳዝን ፍጥረት ... ኤምባሲው በስሩ ላሉ አልሆንላቸው፣ UNHCR ም ቢሆን የፈለጋችሁትን ሁኑ ነው ያለው መጨረሻችን ምን ይሆን?
ሀገር አንገባ እኛስ ጫንቃችን ላይ የተጎበረ ነቀርሳ አለ አይደል? እስከመቼ በመንከራተት እና በስደት እንኑር?

እስኪ

ሰላም ያሰንብተንና እንገናኝ

ቸር

ሰንብቱ